


# ማኅዝዌ

Lesley Koyi
Wiehan de Jager
Dawit Girma
amharisk
nivå 5



በተጨናነቀችው የናይሮቢ ከተማ በርካታ የጎዳና ተዳዳሪዎች ይኖራሉ። የስቃይ ኑሮ በየእለቱ ይገፋሉ፤ እያንዳንዱን ቀን እንዲሁ ይቀበሉታል። አንድ ቀን ጠዋት ልጆቹ ከመንገድ ዳር የተኙበትን ምንጣፍ ጠቀለሉ። ብርዱን ለመከላከል ቆሻሻ አንድደው እሳት ይሞቁ ነበር። ከልጆቹ ውስጥ ማጎዝዌ በእድሜ ትንሹ ነበር።



ወላጆቹ ሲሞቱ ማጎዝዌ ገና 5 ዓመቱ ነበር። ከአጎቱ ጋር ለመኖር ሄደ። አጎትዬው ግን ለልጁ አያስብለትም ነበር። ለማጎዝዌ በቂ ምግብ አይሰጠውም። ከባባድ ስራዎች ያሰራው ነበር።




ማጎዝዌ ካማረረ ወይ ጥያቄ ከጠየቀ አጎቱ ይገርፈዋል። ትምህርት ቤት ለመሄድ ሲጠይቅ አጎቱ ይመታውና እንዲህ ይላል፣ ‹‹አንተ በጣም ደደብ ነህ ምንም መማር አትችልም›› በእንዲህ አይነት ሁኔታ ሶስት ዓመታት ከቆዬ በኋላ አንድ ቀን ሮጦ ከአጎቱ አመለጠ። ጎዳና መኖርም ጀመረ።





የጎዳና ህይወት በጣም አስቸጋሪ ሲሆን ልጆች ምግብ ለማግኘት በየቀኑ ሲለፉ ይውላሉ። አንዳንዴ ይታሰራሉ፣ አንዳንዴ ደግሞ ይገረፋሉ። ሲታመሙ የሚያሳክማቸው ማንም የለም። ልጆቹ ኑሯቸውን የሚገፉት በልመና እና የወዳደቁ እንደላስቲክ አይነት ነገሮችን በመሸጥ በሚያገኙት ትንሽ ገንዘብ ነው። ከከተማው ሌላ ሰፈር ካሉ ሌሎች ጎዳና ተዳዳሪዎች ጋር የተሻለ ለማግኘት የሚያደርጉት ፉክክር ኑሯቸውን ይበልጥ ያመረዋል።



አንድ ቀን ማኅዝዌ የቆሻሻ ገንዳ ላይ እየፈለገ ሳለ አንድ የሆነ የተጎሳቀለና ያረጀ የተረት መጽሐፍ አገኘ። አጸዳዳውና በቦርሳው ከተተው። በየቀኑ መጽሐፉን ያወጣና ስእሎቹን ያያል። ማንበብ ግን አይችልም ነበር።



ስእሎቹ ስለአንድ አውሮፕላን አብራሪ መሆንን እየተመኘ ስላደገ ልጅ ይተርካል። ማኅዝዌ አውሮፕላን አብራሪ የመሆን ነገር እንደቅዠት ያልም ጀመር። በተረቱ ውስጥ ያለው ልጅ ታሪክ የእሱ ይመስለዋል።



ቀዝቃዛ ነበር፤ ማኅዝዌም መንገድ ዳር ቆሞ ይለምናል። አንድ ሰው ወደእሱ እየተራመደ ሄደ። ‹‹ሰላም! ቶማስ እባላለሁ፣ እዚሁ አካባቢ ነው የምሰራው፣ አንተ ምግብ ማግኘት የምትችልበት ቦታ›› አለ ሰውየው። ቢጫ ቀለም ወደተቀባ ባለ ሰማያዊ ጣራ ቤት ጠቆመ። ‹‹ርግጠኛ ነኝ ወደዚያ ሄደህ ምግብ ትለምናለህ?›› ሰውየው ጠየቀ። ማኅዝዌ አንዴ ሰውየውን ቀጥሎ ደግሞ ቤቱን ተመለከተ። ‹‹ምናልባት›› አለ፤ ከዚያም ሄደ።



በቀጣዮቹ ወራት ጎዳና ተዳዳሪዎቹ ልጆች ቶማስን በአካባቢው መመልከት ለመዱ። ቶማስ ከሰዎች ጋር ማውራት ይወዳል በተለይ ከጎዳና ተዳዳሪዎች ጋር። ቶማስ የሰዎችን ታሪክና የህይወት ገጠመኝ ያዳምጣል። ቆፍጣናና ትእግስተኛ ነው፤ ትእቢተኛና ሰው የማያከብር አይደለም። አንዳንዶቹ ልጆች ወደ ቢጫና ሰማያዊው ቤት ምግብ ለማግኘት በእኩለ ቀን መሄድ ጀመሩ።



ማኅዝዌ መንገዱ ዳር እግረኛ መንገድ ጥግ ሆኖ ባለስእል የተረት መጽሐፉን እየተመለከተ ሳለ ቶማስ መጥቶ አጠገቡ ተቀመጠ ። ‹‹ተረቱ ስለምንድን ነው?›› ቶማስ ጠየቀ። ‹‹አንድ ፓይለት ስለሆነ ልጅ ታሪክ ነው›› መለሰ ማኅዝዌ። ‹‹የልጁ ስም ማነው?›› ጠየቀ ቶማስ። ‹‹አላውቅም፤ ማንበብ አልችልም እኮ›› አለ ማኅዝዌ ለስለስ ብሎ።



በተገናኙ ጊዜ ማኅዝዌ ታሪኩን ሁሉ ለቶማስ ያጫውተዋል። አጎቱ እንዴት እንዳደረገው እና እንዴት ማምለጥ እንደቻለ ይነግረዋል። ቶማስ ብዙ አያወራም፣ ማኅዝዌንም እንዲህ አድርግ እንዲያ አታድርግ አይልም፣ ዝም ብሎ በአትኩሮት ብዙ ያዳምጠዋል። አንዳንዴ ባለሰማያዊው ጣራ ትልቁ ቤት ምግብ ሲበሉም ያወራሉ።



የማኅዝዌ 10ኛ ዓመት ልደት ሲደርስ ቶማስ ለማኅዝዌ አዲስ የተረት መጽሐፍ ሰጠው። ዝነኛ እግር ኳስ ተጫዋች ስለሆነ በአንድ መንደር ይኖር ስለነበረ ልጅ ነበር ታሪኩ የሚያትተው። ቶማስ ይህን ታሪክ ለማኅዝዌ ብዙ ጊዜ አነበበለት፤ አንድ ቀን እንዲህ አለው፣ ‹‹እንደማስበው አሁን ትምህርት ቤት የምትገባበትና ማንበብ የምትማርበት ጊዜ ነው። ምን ታስባለህ?›› ቶማስ የልጆች ማቆያና ትምህርት ማግኘት የሚችሉበት ቦታ መኖሩን አብራራለት።



ማኅዝዌ ስለተጠቆመው አዲስ ቦታና ትምህርት ማግኘት ስለሚችልበት ሁኔታ ማሰላሰል ያዘ። አጎቱ ያለው ትክክል ቢሆንስ? ትምህርት መማር የማይችል በጣም ደደብ ቢሆንስ? እዚህ አዲስ ቦታ ከሄደ በኋላ ቢገርፉትስ? መፍራት ጀመረ። ‹‹ምናልባትም እዚሁ ጎዳና ላይ መሆን ሳይሻል አይቀርም›› ብሎ አሰበ።



ስጋቱን ለቶማስ አጋራው። ከጊዜ በኋላ ቦታው ትክክለኛና የተሻለ መሆኑን ቶማስ አረጋገጠለት።



ከዚያም ማጎዝዌ ባለአረንጓዴ ጣራ ቤት ውስጥ ወዳለ አንድ ክፍል ሄደ። ክፍሉን ከሌሎች ሁለት ልጆች ጋር ነው የተጋራው። በቤቱ ባጠቃላይ አስር ልጆች ይኖራሉ። አብረውም ሲሲ እና ባሏ፣ ሶስት ውሻዎች፣ አንዲት ድመት እንዲሁም አንድ ያረጀ ፍየል ይኖራሉ።



ማኅዝዌ ትምህርት ጀመረ፣ ግን ትምህርቱ ትንሽ አስቸጋሪ ሆኖበታል። አንዳንዴ ለማቋረጥ ሁሉ ይመኛል። ነገር ግን አየር አብራሪ እና ታዋቂ ኳስ ተጫዋች የሆኑትን በተረቱ ውስጥ ያሉትን ልጆች ያስባል። ልክ እንደነሱ ትምህርቱን ማቋረጥ የለበትም፣ እነሱ እንደሆኑት ሁሉ ያሰበበት መድረስ ይችላል።



ባለአረንጓዴ ጣራው ቤት ግቢ ውስጥ ቁጭ ብሎ ከትምህርት ቤት የወሰደውን የተረት መጽሐፍ ያነባል። ቶማስ መጣና አጠገቡ ተቀመጠ። ‹‹ተረቱ ስለምን ነው?›› ቶማስ ጠየቀ። ‹‹ታሪኩ አንድ መምህር ስለሆነ ልጅ ነው።›› ማኅዝዌ መለሰ። ‹‹የልጁ ስም ማነው?›› ጠየቀ ቶማስ። ‹‹ስሙ ማኅዝዌ ይባላል!›› አለ ማኅዝዌ በፈገግታ።

# Barnebøker for Norge

barneboker.no

## ማኅዝዌ

Skrevet av: Lesley Koyi
Illustret av: Wiehan de Jager
Oversatt av: Dawit Girma

Denne fortellingen kommer fra African Storybook (africanstorybook.org) og er videreformidlet av Barnebøker for Norge (barneboker.no), som tilbyr barnebøker på mange språk som snakkes i Norge.

Dette verket er lisensiert under en Creative Commons
Navngivelse 4.0 Internasjonal Lisens.